# የግብረ ገብ ሐሳቦች
# በበዓሉ ግርማ ‹‹የህሊና ደወል››[1]

ደሳለኝ ሥዩም (ዶ/ር)[2]

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት ከበዓሉ ግርማ ልቦለዳዊ ሥራዎች አንዱ የሆነውን «የህሊና ደወል» እንደገና ያነባል፤ እንደገና ይፈክራል። የአጥኚው የንባብ ቅኝትም የግብረ ገብ ፍልስፍና ጽንሰ ሐሳቦችን ያማከለ ነው። በተደረገው ቅድመ ጥናት የንባብ ጥረት የህሊና ደወልን ከግብረ ገብ ፍልስፍና አንጻር የተነተነ አጥኚ አለመገኘቱ የዚህ ጥናት አነሳሽ ሰበብ ሆኗል። በመሆኑም ጥናቱ ከዚህ በፊት በሌሎች አጥኚዎች ያልታዩ እይታን ስለመያዙ አጥኚው ያምናል። ይህ ጥናት ዓይነታዊ የጥናት ዘዴን የተከተለ በባህል ጥናቶች (Cultural Studies) የጥናት ንድፈ ሐሳብ የተቃኘና ትኩረቱም የነገረ ግብረ ገብ (Morality) ሐተታና ፍካሬ ነው። ጥናቱ በዋነኝነት ደራሲው በ«የህሊና ደወል» ውስጥ ያነሳቸውን የግብረ ገብ ፈተናዎችና የተጠቀመባቸውን የማርገቢያ ፈሮች ከመሰዋእትነት ምግባራዊ ፍልስፍና (Altruistic morality) ጽንሰ ሐሳብ አንጻር ይተነትናል። በጥናቱ ለመገንዘብ እንደተቻለው የህሊና ደወል ሦስት አንብሮዎችን (Thesis) እንደ መንገድ (Routes) በማበጀት የጠራ የግብረ ገብ ፍልስፍናን ያራምዳል። የመጀመሪያው አንብሮ መስዋዕትነት፣ ሁለተኛው «የፍቅር መሰላሉ ዕውቀት ነው» ሦስተኛው ደግሞ አንድን ተግባር በተገቢው ሰዓት መከወን (ሥራ በጊዜ) የሚሉ መሆናቸው ለማዬት ተችሏል። ይህ የግብረ ገብ ፍልስፍናም በጥቂቶች መስዋዕትነት የብዙኃን ደስታ ለመፍጠር የሚመኘው የመስዋዕትነት ምግባራዊ ፍልስፍና (Altruistic morality) ተመሳስሎሽ መሆኑ ታይቷል።

ቁልፍ ቃላት፡ [ፍልስፍና፣ ግብረ ገብ፣ መስዋዕትነት፣ የህሊና ደወል]

## 1. ዳራ

ሥነ ጽሑፍ ድንበር የማይገድበው ሙያ ነው። ድንበር የለሽነቱ በይዘት፣ በአቀራረብና በዓላማ ጭምር ነው። ድንበር ስለሌለውም የሰውን ልጅ ከባቢና ሁለንታ ይነካካል፣ ይዳስሳል፣ ያምሳል፣ ይፈልሳል። ሥነ ጽሑፍ እንደ አንድ ግዑዝ ነገር በአንድ መልክ ብቻ ሊታይ የማይችለውም ስለዚህ መሆኑን እንደ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001) ያሉ ምሁራን ያስረዳሉ።

---

[1] ይህ ጥናታዊ መጣጥፍ «የግብረ ገብ ሐሳቦች በተመረጡ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች» ከሚለው የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት የወጣ ነው፡፡ አማካሪዎች አየለ ፍቅሬ (ዶ/ር) የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል አአዩ፣ ፋሲል መራዊ (ዶ/ር) ፍልስፍና ትምህርት ክፍል አአዩ፡፡

[2] አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የትምህርትና ባሕርይ ጥናት ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል Dessalegn.seyoum@aau.edu.et ወይም desephilo@gmail.com

በሌላ በኩል ደራሲ የራሱን ዕይታ፣ ያራሱን የዓለም አረዳድ፣ የራሱን የሐሳብ ፍሰት መንገድ ለመጠቀም ነጻነት ያለው ቢሆንም ራሱ ደራሲው የማኅበረሰብ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ነው። በዚህ የተነሣ የተጠየቀውን የመመለስ፣ የተመለሰውን የመጠየቅ፣ የተዳፈነውን የመግለጥ ተገለጠ የተባለውንም እንደገና የመገላለጥ ‹ስልጣን› አለው። Bernstein (1992:1) የጠቀሰው የ Nietzsche ሐሳብ ከዚህ ጋር የሚሄድ ነው።

> Very early in my life I took the question of the relation of art to truth seriously: even now I stand in holey dread in the face of this discordance.
>
> ከወጣትነቴ ጀምሮ ራሴን የምጠይቀው ጥብቅ ጥያቄ በጥበብና በእውነት መካከል ያለውን ግንኙነት ነው። ዛሬም ላይ ሆኜ እንኳ ለጥያቄው ያለኝ ምላሽ ወላዋይነት ነው።

ደራሲው የሚጽፈው የሠራውን ማኅበረሰብ ለመግለጽ ወይም በሠራው ማኅበረሰብ ላይ ለማመጽ ነው። እውነቱ ይህ ከሆነ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ማኅበረሰብን እናያለን። በአንድ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ ማኅበረሰቡን ወይም ማኅበረሰባዊ እውነታዎችን እናያለን ስንል ግን ነገሩ የፍካሬ እንጅ ጥሬ ሀቅ የመቁጠር ጉዳይ አይደለም። Bernstein (1992:2) ሥነ ጽሑፉን በመፈከር እውነቱን መመርመር ካልሆነ በቀር እንደ የቀመር ሳይንስ (Natural Science) የሚለካ፣ የሚመዘን፣ የሚበዬን፣ የሚዳኝ እውነት በቀጥታ ማግኘት አዳጋች ስለመሆኑ ያስረዳሉ።

ሥነ ጽሑፍ ትኩረት ከሚያደርግባቸው የሰው ጠባያት ወይም የማንነት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ ነገረ ግብረ ገብ ነው። ነገረ ግብረ ገብ የሥነ ጽሑፍ ተግባር ነው ስንል ግን የሥነ ጽሑፍ ግብሩ «ሰባኪነት» ነው ወደሚል ቁንጽል ምልከታ የሚወርድ አይደለም። ሥነ ጽሑፍ ነገረ ግብረ ገብን ጉዳዬ ብሎ ሲነሣ መስበከን የመጨረሻ ግቡ አድርጎ አይደለም። ይልቁንም ራሱ ግብረ ገብ ምን እንደሆነ ለመፈከር፣ ለመመርመር እና ለመዘርዘርም ጭምር እንጅ።

ደራስያን በምናባቸው ዓለምን ይፈጥራሉ ሲባል ሥነ ጽሑፍን ይከውናሉ ማለት ነው። ሥነ ጽሑፍን መከወን ደግሞ ከዘገባ ይለያል። ደራሲው አንድ የሚያየውን ገጠመኝ መነሻ ቢያደርግ ገጠመኙን እንደወረደ የመዘገብ ሥራን አይሠራም። ይልቁንም የሰው ልጆች ሁሉ ወላዊ ወደሆነ እውነታ አሳድጎ ይፈትተዋል፤ ይተነትነዋል፤ ይፈክረዋል እንጅ። አንድን ገጠመኝ ወደ ወላዊ የሰው ልጅ እውነትነት ለማሳደግ ደግሞ ደራሲው «ገናን እውነታዎችን» ይመርጣል። ከእነዚህ ገናን እውነታዎች ደግሞ ነገረ ግብረ ገብ ይጠቀሳል።

ነገረ ግበረ ገብ ፈርጀ ብዙ ነው። በፈርጀ ብዙነቱ ቀላልና ከባድ፣ ሰፊና ጠባብ፣ ነጠላና ጥቅል ጉዳዮችን ያያል። ሥረ ብዙም ነው። በሥረ ብዙነቱ ሃይማኖታዊ ወይም ማኅበራዊ፣ ግላዊ ወይም ማኅበረሰባዊ፣ ባህላዊ ወይም ፖለቲካዊ፣ ወዘተ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ ጠባይን፣ ግብርን፣ እውቀትን እና የመሳሰለውን የሚጠቀልል መሆኑ ፈርጀ ብዙ ያደርገዋል። በዚህ ረገድ የአማርኛ

ልቦለዶችን ከነገረ ግብረ ገብ አንጻር ያጠኑ ጥናቶች እንዳሉ ፍለጋ አካሂጃለሁ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማግኘት የተቻለው "The Changing Face of Moral Vision in the Amharic Novel" በሚል ርዕስ ጠና ሻሌ በ2007 እ.ኤ.አ. ያጠናቀረው ለውጭ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት እንዲሁም «ገጸ ክርስቶስ በበዓሉ ግርማ ቅድመ አብዮት ኖቨል» በሚል ርእስ ኤልያስ አያልነህ በ2000ዓ.ም ያሳተመው ጥናታዊ መጽሐፍ ናቸው።

በጠና ጥናት ውስጥ የተካተቱት መጻሕፍት የስድስት ደራስያን ልቦለዳዊ ሥራዎች ሲሆኑ በሃምሳ ዓመታት ውስጥ የተጻፉ እና በአቀራረባቸው ልዩ ልዩ የሆኑ ልቦለዶች ናቸው። ጠና በጥናቱ ውስጥ ለማሳዬት የሞከረው ሞራል በፊውዳሉ ዘመን (በሀዲስ ዓለማየሁ ሥራዎች)፣ ሞራል በነባሩ እና በአዲሱ ትውልድ (በዳኛቸው ወርቁ ሥራ) ሞራል በመደባዊ አስተሳሰብ (በበዓሉ ግርማ ሥራዎች) ሞራል በብሔረሰባዊ አስተሳሰብ (በተስፋዬ ገብረ አብ ሥራ) ሞራል እንዲሁም የተሻሻሉ የሞራል ጉዳዮች በፍቅረ ማርቆስ ደስታ እና ሂሳይ ንጉሡ ልቦለዶች ውስጥ ለማሳዬት ሞክሯል።

የጠና የምርምር ሥራ ሞራልን ጉዳዬ ብሎ ለማዬት የተጠና ይሁን እንጅ ከእኔ ጥናት የትኩረት ነጥብ አንጻር ሲታይ የሚገናኝ አይደለም። እኔ የማነሣው ግብረ ገብን ራሱን ሳይሆን የግብረ ገብ ፍልስፍናን በመሆኑ ነው። በሌላ በኩል ኤሊያስ አያልነህ ለእንግሊዘኛ ሥነ ጽሑፍ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የሠራውና «ገጸ ክርስቶስ በበዓሉ ግርማ ቅድመ አብዮት ኖቨል» ብሎ ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥ ሀዲስ ሳህሌን ከመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እያነጻጸረ አቅርቧል። ንጽጽሮቹም የሀዲስን ተግባራት፣ እምነትና እጣ ፈንታ ከክርስቶስ ጋር ማነጻጸር ነው። ለቁሳዊ ነገሮች ሚዛናዊ አመለካከት ያለው፣ ልበ ሙሉ ነጻ አውጭ፣ እጅግ አዛኝና ሩህሩህ፣ ድንቅ መካር፣ ታላቅ መምህር፣ መሪና አዛዥ፣ እጅግ ለጋስና እውነተኛ ፈራጅ፣ ወደር የለሽ ነቢይና እንከን የለሽ የፍቅር ምሳሌ እያለ ያነጻጽረዋል። ይህም ቢሆን ከእኔ የጥናት ትኩረት ጋር ልዩነት አለው። እኔ «የህሊና ደወል»ን የማጠናው ስለ ነገረ ግብረ ገብ ፍልስፍናዊ ጉዳይ ነው። የእኔ ጉዳይ ይህንን ፍልስፍናዊ ጉዳይ በ «የህሊና ደወል» ረጅም ልቦለድ ውስጥ መመርመር ነው የጥናቱ ዓላማም በተመረጠው ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ ያሉ የግብረ ገብ ሐሳቦችን ምንነት፣ ዓይነትና እንዴትነት ከግብረ ገብ ፍልስፍና አንጻር መተንተን ነው።

## 2. ጽንሰ ሐሳቦች

ከምግባር ፍልስፍና ሦስት ዘርፎች ማለትም ከዲበ ምግባራዊ ፍልስፍና (Meta Ethics)፣ ከተግባራዊ ምግባር (Applied Ethics) ውስጥ አንዱ የሆነው የዕለት ወይም መመሪያዊ ምግባር (Normative Ethics) አንዱና ዋነኛው የግብረ ገብ ፍልስፍና ነው። ይህ ዘርፍ የግብረ ገብ ፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ የሆነውን «ሰዎች ምን ማድረግ አለባቸው?» የሚል ጥያቄ የሚያነሣ፣ ሥርዓታዊ የሆነ የድርጊት ማዕቀፍን ለማነጽ የሚሞክር የፍልስፍና ዘርፍ ነው።

ዋነኛ ትኩረቱም ትክክል የሆነውን ስህተት ከሆነው የምንለይባቸውን የግብረ ገብ መርሖዎች (Moral Principles) መለየትና መሞገት ነው። William (1973፡2) እንደሚለው የዕለት

ወይም መመሪያዊ ምግባር ፍልስፍና የግብረ ገብ ብያኔዎችን ይዞት የሚመለከት ሲሆን ልክና ስህተት የምንላቸውን ፍረጃዎች መስፈርት ይፈልግላቸዋል።

ከዚህ ሐሳብ ጋር ስውር በሆነ መንገድ ሐሳቡና የሚያቀርበው Shafer-Landau (2015) የዕለት ምግባር ፍልስፍና ድርጊትን የሚሠሩ መርሖዎችን ለማግኘት የሚጥር ዘርፍ ስለመሆኑ ያትታል። እነዚህ መርሖዎች ከግብረ ገብ አንጻር ትክክልና ስህተት የሆኑትን፣ ግዴታዎችንና የተፈቀዱትን ነገሮች እንዲሁም መልካሙንና እኩዩን ይነግሩናል ይላል።

በዚህ የፍልስፍና ዘርፍ ይበልጥ ትኩረት የሚሠጣቸው ፍልስፍናዊ ጥያቄዎች፣ «ምንን እንዴት አድርጎ መከወን ነው ልክ? መልካም ሕይወት እንደምን ያለ ነው? ለሌሎች ያለን የግብረ ገብ ግዴታ እስከምን ድረስ ነው? የግብረ ገብ ትክክለኝነት የሚወሰነው በምን መሥፈርት ነው?» የሚሉት ይገኙበታል።

የግብረ ገብ ልክነት መሥፈሪያው ወይም መለኪያው ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ የእለት ወይም መመሪያዊ ምግባር ፍልስፍና ዋና ዋና ጽንሰ ሐሳቦች መሠረት ሆኖ ይገኛል። ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡ ልዩ ልዩ ምናልባትም ተጻራሪ ምላሾችም በጥቅሉ የነገረ ግብረ ገብ ዋነኛ የክርክር ነጥቦች ሆነው ቀጥለዋል። ቀጥሎ የጽንሰ ሐሳቦቹን የሚያቀነቅኑ ዋና ዋና ፈላስፎች ያነሷቸውን ሐሳቦች በዐጭሩ እንመልከት።

### 2.1 ኃላፊነት ተኮር (Deontology)

«ኃላፊነት» አንደኛው የእለት/መመሪያው/ ምግባር ፍልስፍና የሙግት መሰረት ነው። የጽንሰ ሐሳቡ ትኩረቱ የግብረ ገብ መሥፈሪያ (መለኪያ) ድርጊቱ በሚያስገኘው ውጤት ላይ ሳይሆን ድርጊቱ ራሱ በሆነበት ትክክለኝነት ላይ ነው። እንደዚህ ጽንሰ ሐሳብ አራማጆች ከሆነ የግብረ ገብ ሕግጋት መሰረት ሊሆን የሚገባው በነገሮች ያልተመሰረተ ኃላፊነት (Duty) ስለመሆኑ ኢማኑኤል ካንትን የመሰሉ ፈላስፎች ያስረዳሉ።

በስሜት እና ሊያስገኝ በሚችለው ጥቅምና ጉዳት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ግን የግብረ ገብ ጥያቄነቱ በራሱ አብቅቷል የሚል መደምደሚያ አላቸው። አንድ ትክክል ያልሆነ ወይም እኩይ ነገር ጥቅም የሚያስገኝ ስለሆነ ወይም ጥሩ ስሜትን የሚፈጥር በመሆኑ ብቻ ድንገት ተነሥቶ ትክክል ወይም መልካም ሊሆን አይችልም።

እንዲህ ያለው ጽንሰ ሐሳብ የግብረ ገብ ትርጓሜ እስከ ጭራሹ ባዶ የሚያደርግ ነው ይላሉ ፈላስፎቹ። የዚህ ጽንሰ ሐሳብ ዋና አቀንቃኝ የሆነው Kant (1938፡3) 'Ground work of metaphysics of morals' በሚለው ሥራው «ከማደርገው ድርጊት የሚመነጨው መርህ ሁለንተናዊ መርህ (ሕግ) እንዲሆን የምፈቅደው ዓይነት እስካልሆነ ድረስ ያደረግሁት ነገር ትክክል ነው ሊባል አይችልም» የሚል ሐሳብ ያነሳል።

የKantን አባባል በምሳሌ ለማየት ቢሞከር ለምሳሌ አንድ የመዋሸት ድርጊት ትክክል ነው ማለት የምንችለው ከድርጊቱ የሚቀዳው «መዋሸት ተገቢ ነው» የሚለው መርህ (maxim) ሁለንተናዊ ሕግ (universal law) እንዲሆን መፍቀድ ስንችል ነው። ያ ማለት ሁሌም በምንም ሁኔታ ውስጥ ማንም ቢዋሽ መዋሸት ትክክል ነው ብሎ መቀበል ግዴታ ነው። ነገር ግን ይሄንን መቀበል አለመቻላችን ብቻ ሳይሆን ችግሩ እነዚህ መርሖዎች ዓለማቀፋዊ ቢሆን በራሱ መርሆዎቹ ተግባራዊ መሆን አይችሉም። ሁሉም ሰው እንዲዋሽ በአዋጅ የታወጀ ያህል በሚሆንበት አውድ ውስጥ እምነት የሚባል ነገር ጨርሶ ሊኖር አይችልም። እምነት የውሼት ተቃኒ በመሆኑ። ያለ እምነት ደግሞ ውሸት እራሱ መቀጠል አይችልም። እምነት የውሼት ማንጸሪያ፣ እምነትም የውሼት ማንጸሪያ ናቸውና። መዋሼት ሁለንተናዊ ሕግ ቢሆን ውሸት የሚባለው ነገር በራሱ አይኖርም። ምክንያቱም ውሸት የተመሠረተው በመደበቅ ላይ በመሆኑ ነው።

### 2.2 የርትዕ ምግባር (Virtue ethics)

ርትዕእ ሌላኛው የሙግት መሠረት ነው። የርትዕ ምግባር የግብረ ገብ ፍልስፍናን ያክል ዕድሜ ያስቆጠረ ሲሆን ከዘርፉ ጀማሪዎች መካከል በቀደምቶቹ ፕሌቶና እና አርስቶትል ጭምር ይቀነቀን የነበረ የግብረ ገብ ፍልስፍና ዓይነት ነው። የርትዕ ምግባር መርህ የመልካምነትና የእኩይነት መርህ በሕግና በትምህርት የሚገኝ ሳይሆን በሁላችንም ሰብዕና ውስጥ ተቀብሮ ያለ፣ ወደ ርትዕ በቀረብን መጠን የሚገለጥም ነው ይላሉ።

> የርትዕ ምግባር በሰው ልጆች ሁላዊ ሰዋዊነት ላይ ያተኩራል እንጅ አንድ ውስን የሰው ልጅ ተግባር ላይ ብቻ የሚያተኩር አይደለም። በዚህ መሠረት እንደ ሀቀኝነት፣ ክብር፣ ብርታት፣ ለጋስነት፣ ታማኝነት፣ ሚዛናዊነት፣ ራስን መግዛትና ሁላዊ ጥበብ የግብረ ገብ ንድፈ ሐሳብ እምብርት ይሆናሉ[3]

ይህ ማለት የርትዕ ምግባር በተናጠል ከሚፈጠሩ ሁነቶች እና ድርጊቶች ይልቅ የግለሰቡ ሙሉ ሰብዕና ላይ የሚያተኩር መሆኑን የሚገልጽ ነው። እንደ ልግስና፣ ታማኝነት እና ራስን መግዛት ያሉ የሰብዕና መገለጫዎች በግለሰቡ ላይ በሰፈኑ መጠን አንድ የተደነባ ደንብን መከተል ሳያስፈልገው ወይም ለአንዳች ሕግ ስለመገዛት ሳይጨነቅ የድርጊቱን ውጤት ማስላት ሳይጠበቅበት መልካምና እኩዩን ለመለየት ለይቶም ለመተግበር ያስችላል የሚል ነው የፍልስፍና መሠረቱ።

---

[3] ‘Virtue ethics is concernd with the whole of person’s life, rather than a particular episode or action. If regards the virtue (such as honsity, courge, compassion, generosity, fidelity, fairness, self-control, providence) as central to moral theory. Rosalind Hursthouge, 1998, Virtue Ethics, Stanford encyclopedia of Philosophy (online published).

### 2.3 እኔያዊ ምግባር (የግል ጥቅመኝነት) (**Ethical Egoism):**

እኔያዊ (የግል ጥቅመኝነት) የጥቅማዊነት (Telelogical ethics) አንዱ ዓይነት ሲሆን የድርጊቶችን ግብረ ገባዊ ዋጋ ወይም ትክክለኝነትና ሥህተትነት መወሰኛ መርሁ የግልሰቦች ጥቅም ነው የሚል መከራከሪያ ነው። ከወል ጥቅማዊነት (utilitarianism) በተለየ የግል ጥቅማዊነት የድርጊቶችን ውጤት ጠቃሚነት እና ጎጅነት በቀጥታ ከድርጊቱ ፈጻሚ ግለሰብ ጋር ብቻ በማገናኘት የሚሞግት ስለመሆኑ እንደ Sidgwick (1874) ያሉ ጸሐፍት ያትታሉ።

ሰዎች በተፈጥሯቸው የራሳቸውን ፍላጎት የሚያስቀድሙ ራስ ወዳድ ናቸው ከሚለው ሥነ ልቦናዊ ጥቅማዊነት (Psychological egoism) በተለየ ምግባራዊ ግላዊ ጥቅመኝነት (Ethical Egoism) ይህ የሰዎች ተፈጥሯዊ ሁኔታ የግብረ ገብ መርህ መሆን አለበት ይላል።

ስለዚህ ሰዎች በተፈጥሮ ራስ ወዳድ ናቸው ማለት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ የሰው ልጅ ድርጊት የግል ፍላጎትን ያስቀደመ ራስ ወዳድነት ያለበት መሆን አለበት የሚል ሙግት ነው። በ Rachel (2003:63) '….ethical egoism is a doctrine that each person ought to pursue his or her own self-interest exclusively' ይላሉ። እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱን መሻት ብቻ ሊከተል ይገባል እንደማለት ነው። ስለዚህም የሰዎችን ተፈጥሮ ከማብራራት አልፎ ራስ ወዳድነት ወይም የራስን ጥቅም ከሁሉ አስቀድሞ መመልከትን የግብረ ገብ ዋጋ (Moral Worthness) መስፈሪያ አድርጎ ይመለከታል።

Rand (1964:4) "man – every man is an end in himself, not the means to the end of others" የምትለው አገላለጽ በተለይ ከመስዋዕትነት ግብረ ገብ (altruistic morality) በግልጽ የተቃርኖ ጽንፍ የሚቀመጥ ነው። ሁሉም ሰው በራሱ የነገሮች ሁሉ የመጨረሻ ግብ ነው እንጅ ለሌሎች ጥቅም ማሟያ መንገድነት ማገልገል የለበትም የሚለው የኢጎይስቶች እይታ ማንኛውም ሰው የራሱን ደስታና ጥቅም ለማስጠበቅ መስራት እንዳለበት ይሄንንም ማድረጉ ልክ መሆኑን የሚሞግት ነው።

ከወል ጥቅማዊነት በተለየ ሁኔታ የብዙኃን ደስታ ወይም ጥቅም እንደ ድርጊቶች የግብረ ገባዊነት ዋጋ ሚዛን አድርጎ አይመለከትም። ይህንን ጉዳይ Sidgwick (1874:417) ሲያብራራ "Egoism directs me to seek my won greatest happiness; utilitarianism is, the greatset happiness of greatset number" . ይላል። «የወል ጥቅመኝነት ለብዙኃን የበዛውን ደስታ እንድፈልግ ሲነግረኝ ግላዊ ጥቅማዊነት ግን ለራሴ የበለጠውን ደስታ እንድሻ ይመክረኛል» የሚለው የሲድዊክ አቋም ሰዎች ምንጊዜም አንድን ድርጊት ከመፈጸማቸው በፊት ማሰብ ያለባቸው ብቸኛ ነገር ‹የድርጊቱ ውጤት ለእኔ ደስታን ይሰጠኛል፤ ጥቅም ያስገኘኛል?› ብለው መሆን አለበት የሚል መከራከሪያ ነው።

## 3. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ሥነ ጽሑፋዊ ጥናት በዓይነታዊ የጥናት መደብ ውስጥ የሚካተት ነው። ጥናቱ ፍካሬያዊ ጥናት ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ሀተታዎችን፣ የገጸ ባህርያት ንግግሮችንና ድርጊቶችን በመፈከር በመጽሐፉ ውስጥ የታዩ የግብረ ገብ ፍልስፍና ሙግቶችን ለይቶ ያሳያል። ጥናቱ መደገፊያ የሚያደርገው የሥነ ጽሑፍ ጥናት ንድፈ ሐሳብ የባህል ጥናቶች ንድፈ ሐሳብን ነው። የባህል ጥናቶች ንድፈ ሐሳብ ከጊዜ ጊዜ ድንበራቸው እየፈራረሰ እና የጥናት ወሰናቸው እየተቀራረበ ለመጡት እንደ ሥነ ጽሑፍ፣ ፍልስፍና፣ ሥነ ባሕርይ፣ ሥነ ሰብ፣ ሥነ ማኅበረሰብ፣ ፎክሎር፣ እና የመሳሰሉት የሰብአዊነትና የማኅበራዊ (Humanties And Social Sciences) ጥናቶች እያገለገለ ያለ ንድፈ ሐሳብ ነው።

ንድፈ ሐሳቡ ግለሰብ በቡድን (ማኅበረሰብ ውስጥ) የሚኖረውን ተሳትፎ ወይም ተጽዕኖ ለማዬት የሚያስችል ነው። የግብረ ገብ ፍልስፍና አንድ ግለሰብ በማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖረውን ሁለንተናዊ ተሳትፎ የምንመለከትበት፣ የምንለካበት፣ የምንተችበት እና ደረጃ የምናበጅበት ነው። ስለዚህ ይህ ንድፈ ሐሳብ ይሄንን የምርምር ሥራ ለመሥራት ሁነኛ መመርኮዣ ሆኗል።

በትልቅ ማኅበረሰባዊ ውቅር ወይም ቡድናዊ አደረጃጀት የተነሣ በአንድ ግለሰብ ወይም በጥቂት የግለሰቦች ንዑስ ጥምር ላይ የሚደርስን ተጽእኖ፣ ፈቃድና አረዳድ ለመፈተት የሚጠቅም ንድፈ ሐሳብ በመሆኑ ነው። ነገረ ግብረ ገብ አንድ ግለሰብ በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖረውን ሁለንተናዊ ተሳትፎ የምናይበት ብቻ ሳይሆን ያ ማኅበረሰብ የሚሠራቸው የሥነ ምግባር ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ልማዶችና ሕጎች በግለሰቡ አእምሯዊ፣ አካላዊና ጠባያዊ ማንነት ላይ የሚኖራቸውንም ተጽዕኖ የምናይበት ፍልስፍና እንደመሆኑ ይህ ንድፈ ሐሳብ ይሄንን የምርምር ሥራ ለማከናወን ዓይነተኛ መንገድ ሆኖ አገልግሏል።

ነገረ ግብረ ገብ አንድ የፍልስፍና ዘርፍ ይሁን እንጅ የሰው ልጅን ማንነት ከሚቀርጹት ትውፊት፣ ሃይማኖት፣ ማህበራዊ ሥሪት፣ ኪነ ጥበብ፣ ሥነ ልቡና፣ መልከዓ ምድር፣ አፈታሪክ እና ሥነ ትምህርት ጋር የሚገናኝ ነው። ግብረ ገብ በሌላ መልኩ የአንድ ግለሰብ መታወቂያ ማንነት የሚሆነውም በዚህ የተነሣ ነው። የማንነት መታወቂያ ስለሆነም ማንነት (Identity) ላይ የተመሠረተ ሥነ ጽሑፋዊ ትንታኔ ለማድረግ በማሰብ ከሥነ ጽሑፍ ጥናት ንድፈ ሐሳቦች መኻል የባህል ጥናቶች ንድፈ ሐሳብን እንዲሁም ከአትኩሮት አንጻር የእለት (መመሪያዊ) የምግባር ፍልስፍናን ጠገግ በማድረግ ነገረ ግብረ ገብን በተመረጠ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች ውስጥ ለመመልከት ተሞክሯል።

ልቦለዱ በተመረጠው ርእሰ ጉዳይ፣ በተመረጠው ንድፈ ሐሳብ እና የጽንሰ ሐሳብ ማዕቀፍ ለማዬት፣ የይዘት ትንተና ለማድረግ የሚመች መሆኑን በመለዬት ዓላማ መር የሆነ የናሙና መረጣ ዘዴ የተመረጠ ነው።

«የህሊና ደወል» የአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ ተማሪዎች ባነሱት አመጽ ሳቢያ ለአንድ አመት የተቀጣው ሀዲስ ደሃ እናቱን ለማገዝ ለራሱም ልብስና መሰል ፍጆታውን ለመሟላት ለአንድ ዓመት

የሚሆነውን ሥራ ሲፈልግ ወደ ሱጼ ቦሩ ሄዶ ለአንድ ዓመት በመምህርተነት እንዲያገለግል እድል የሚያገኝበት ልቦለድ ነው። ሀዲስ ወደ ሥፍራው ከመንቀሳቀሱ በፊት ግን እናቱ ታምመው ያርፋሉ። በግማሽ ልብ ወደ ሱጼ አቅንቶ ከትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር አቶ ይርጋ ጋር በሚያደርገው ክርክር ታሪኩ ይጀምራል።

ለአንድ ዓመት አስተምሬ ጥቂት ሳንቲም ይዤ በመመለስ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን እቀጥላለሁ የሚል እምነት ነበረው። ነገር ግን የሱጼ ቦሩ ትምህርት ቤት ለማስተማር ምቹ ሁኔታ የሌለበት፣ ትምህርት ቤቱ የፈራረሰ መምህራኑ ሞራላቸው የተዳከመ፣ ባለህበት ሂድ የሚረግጡ ሆነው አገኛቸው። ባንጻሩ ብዛት ያላቸው ተማሪዎች ደግሞ በአስተማሪና በመማሪያ ክፍል እጥረት መማር እንደተቸገሩ ያያል።

በእንግድነት ያረፈባት አንድ መሽታ ቤት ያገኛት ሽታዬ የተባለችን ሴት እየያዘ መተኛት የጀመረው በዚህ ሰሞን ነበር። በሌላ በኩል በቀዬው ተደማጭነት ያላቸው ፊታውራሪ ተካ አሉ። ህዝብ ይፈራቸዋል፤ ያከብራቸዋል። ችግሩንም ደስታውን ያካፍለቸዋል። በዚህ ሁኔታ በእንግድነት ያገኛቸው ሀዲስ ከእሳቸው ጋር ሲጨዋወት ተራማጅ ሐሳብ ያላቸው መሆናቸውን በንግግራቸውም በሥራቸውም ያጤናቸዋል። እሳቸውን የመሰለ ቅን አሳቢ አገልጋይም አላቸው። ከዚህም በቀር ዓይናለም የተባለች ቆንጆና አስተዋይ ልጅ አለቻቸው።

የትምህርት ቤት ግንባታ በራሳችን አቅም መስራት ይገባናል ብሎ ሀዲስ ሲነሳ አቶ ይርጋ ከፖሊስ አዛዡ ጋር በመሆን አድማ ይመታሉ። ሀዲስ ከፊታውራሪ ጋር ይሰለፋል። አዲስ ትምህርት ቤት እንስራ የሚለው የሀዲስ ሐሳብ አሸናፊ ሆኖ ቡና ለቃሚዎች ሳይቀሩ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ገንዘብ ያዋጣሉ። የአዲሱ ትምህርት ቤት ስራም በደምብ ይቀጥላል።

የፊታውራሪ ተካ አገልጋይ በአይናለምና በሀዲስ መሃል መልዕክተኛ ሆኖም የልብ አውቃነቱን ያስመሰክራል። ከሀዲስ ጋር ሲጨዋወቱ ለአንድ ዓመት ብቻ ሊሰራ እንደመጣ ይገነዘባል። በመካከል ሀዲስ ወደ ከተማ ደርሶ ለመመስ ከሱጼ በራቀበት አንድ ቀን አንድ ክስተት ተከሰተ። አቶ ይርጋ ተገደሉ። ሽታዬም ገዳዩ ሀዲስ መሆኑን የአይን እማኝ ነኝ ብላ በመስከሯ በሀዲስ ላይ የሞት ፍርድ ሊፈረድ ጫፍ ደረሰ። በዚህ ጊዜ ግን የፊታውራሪ አሽከር ቶሎሳ አላስቻለውምና ገዳዩ ራሱ መሆኑን ይህንም ያደረገው አቶ ይርጋ ከተወገዱ ሀዲስ የእሳቸውን ቦታ እንደሚይዝና ለሱጼ ህጻናትም ብዙ የሚጠቅም ስራ እንደሚሰራ በማመኑ መሆኑን ተናግሮ በሃዲስ ቦታ ይታሰራል። ሽታየ ለምን በሀሰት እንደመሰከረች ስትናገርም አይናለምን ይወዳታል እኔ ግን ሊያገባኝ እፈልግ ነበር ህልሜን ስላጨናገፈው ነው ትላለች። ለጥፋቷም በእስራት ትቀጣለች።

ትምህርት ቤቱ ግንባታው ቀጥሎ አይናለም የአንገት የወርቅ ሀብሏን ታዋጣለች። በሀብሉም ለትምህርት ቤቱ ደዎል እንዲያስራበት ለሀዲስ አደራ ትለዋለች። በስተመጨረሻ ትምህርት ቤቱ ተሰርቶ ይጠናቀቃል። ሀዲስ ቃል በገባው መሰረት በሀብሉ ገንዘብ ደወል አሰርቶ ሰቀለ። ከአይናለም ጋር አብረውም የትምህርት ቤቱን መጠናቀቅ የሚያበስር ደወል ደወሉ፤ ፊታውራሪ ይሄንን ደስታ አይተው ሲያርፉ ታሪኩን የሚደመድም ልቦለድ ነው።

## 4. ትንታኔ

የ«ህሊና ደወል» ታሪክ መነሻ ሱጴ ወረዳ እልቂ ማርያም ትምህርት ቤት ነው። አቀንቃኙ ገጸ ባህርይ ሀዲስ ሳህሌና ጸረ አቀንቃኙ አቶ ይርጋ ዓለሙ በሚያደርጉት ክርክር ቀመስ ውይይት ታሪኩ ይጀምራል። ይህ ሁለቱን ገጸ ባህርያት ሳያግባባ ውይይት የሚያስጀምር ነጥብ የትምህርት ቤቱ ማርጀትና በጠቅላላው እንደ ሥርዓት በቀጠሉት ውስብስብ ችግሮች ላይ ሁለቱ ገጸ ባህርያት ያላቸው የአረዳድ ልዩነት ነው።

ሀዲስ ሳህሌ ባለው ሥርዓት መቀጠል እንደማይችል ይናገራል፤ አንዳች አዳስ ነገር መሥራት እንደሚገባ ይሞግታል፤ በዚህ ሁሉ መሃል ምቾት የማጣት ስሜት እየተጠናወተው እንደሆነ ደጋግሞ ይናገራል። በሌላኛው ጽንፍ አቶ ይርጋ ዓለሙ በነባሩ ሥርዓት ምቾት እንዳላጡ ይልቁንም አጉል መንፈራገጥ ለመላላጥ መሆኑን ደጋግመው ይናገራሉ። በቀጣይ ታሪኮች ሀዲስ ሳህሌን በአቋም የሚመስሉት ፊታውራሪ ተካ እንዲሁም ለእነዚህ ሰዎች አቋም መስዋዕት ለመሆን ያልሰሰተው ቶሎሳ በአንድ ወገን፣ በሌላኛው ወገን ደግሞ ግላዊ ጥቅምን ያማካለ ሩጫን የሚሮጡት የመቶ ዓለቃ አሽኔ እና አቶ ይርጋ አለሙ እስከ መጽሐፉ ፍጻሜ ድርስ በተጻራሪ ወገን ሆነው ሙግታቸውን ይቀጥላሉ።

የታሪኩ ትውስብ የሚነሳውም ሀዲስ አዲስ ትምህርት ቤት በራሳችን አቅም እንገንባ፣ አዲስ ዘመኑን የሚመስል ሥርዓት እናቁም ሲል የእነ አቶ ይርጋ ወገን ደግሞ ትምህርት ቤቱና የትምህርት ሥርዓቱ የግል ጥቅምን ካልነካ በቀር ለትውልድ ይህ ነው የሚባል ነገር ስለመሠራት አለመሥራቱ አይጨነቁም። የአቶ ይርጋ ሙግት ጥቅሜ አይጓደል የሚል ሲሆን የሀዲስ ሙግት ግላዊ ጥቅም አብቀቶ ለትውልድ የሚቆይ ሥራ መሥራት ይገባናል የሚል ነው። በስተመጨረሻ ሁለቱም ወገኖች ለየዓላማቸው ተጉዘው የሀዲስ አቋም አሸናፊ ሆኖ አዲሱን ትምህርት ቤት ሰርቶ ሲያቆም የምናይበት መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ደራሲው በዓሉ ግርማ የግብረ ገብ ጉዳዮችን በገጸ ባህርያቱ በኩል እያሄደ በትረካው በኩል እያጎላመሰ ያስነብባል። በ«የህሊና ደወል» ውስጥ ደጋግሞ እንደሚስተጋባው የግብረ ገብ ፍልስፍና መሠረቶቹ የሚከተሉት ቁም ነገሮችን የሚታከክ ነው።

> **እምነት፡** ሰው ሲባል ሕይወቱን የሚመራበት አንድ እምነት እንዲኖረው ያስፈልጋል። እምነት የሌለው ሰው በድን ነው፤ ከእንስሳ አይሻልም (ገጽ 122)
>
> **ኅሊና፡** ህሊና ወደ መራን መንገድ የግድ መሄድ ይኖርብናል (ገጽ 143) ሰበብ ህሊናን መግደል የለበትም (ገጽ 9)
>
> አንሻልም ያለ ፍቅር። ህሊናችን ያንቀላፋል ወኔያችን ይሸናል። እምነታችን ያወላውላል። እምነቱ የሚያወላውልና ራሱን ወዳድ የሆነ ትውልድ ምንጊዜም ቢሆን ህዝቡን ሊለውጠው አይችልም ገጽ (177)

**እውቀት፡** የፍቅር መሰላሉ እውቀት- የእውቀት መሠረቱ ደግሞ ትምህርት ቤት ነው (ገጽ 145)

**እጅ** ((*ሥራ*)(**ተግባር**))፡ አፈወርቅ ተክሌ የሚስላቸውን ጣቶች ይመስላሉ። ውብ አለንጋ መሳይ። ግን ምን ያደርጋል። የህሊና ዝገት ምልክት መስለው ነው የሚታዩኝ» (ገጽ181) «አሁንም ቢሆን እኔ የማምነው ከብዙ ምላስ በትንሽ *ሥራ* ነው» (ገጽ 178) «የሰው ልጅ ካለው ታላላቅ ጸጋዎች ውስጥ አንዱ እጅ ነው። እጄን ለሥራ እንጅ ለጥፋት ዘርግቼ አላውቅም (ገጽ 185)

**ጊዜ፡** ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ ጊዜን ድል ለማድረግ ከመሞከር ቦዝኖ አያውቅም። ግን ጊዜን ድል ማድረግ የሚቻለው ጊዜን በማክበር ብቻ ነው። ህልውና ማለት ራሱ ጊዜ ነው-ከጊዜ **ፍቅር፡** ከሚጮህ ናስ

ውጭ የሆነ ነገር ከዚህ አለም አይደለምና» (ገጽ 32) «ሰው ማንነቱና ትልቅነቱ እንዲሁም ስለሌላው ያለው በጎ ፈቃድ ርህራሄና አሳብም ጭምር የሚገመተው በቀጠሮ ሰዓት አክባሪነቱ ነው (ገጽ 103)

ይህ ጥናት መታገኒያ ያረገው «የባህል ጥናቶች» ንድፈ ሐሳብ አንደኛው ትኩረት «ምንነት» እና «ማንነት» ማተኮር ነው። እንደ ምንነት የትኩረት ነጥብ በበዓሉ ሥራዎች ውስጥ «እውቀት» «ፍቅር» «ህሊና» «እምነት» ቦታ ተሰጥቷቸው ይተነተናሉ። እንደማንነት ትርጓሜ ደግሞ «በጊዜ ሥራን የሚሰራ ሰው» ማንነት በጉልህ ተስሏል። በሌላ በኩል በጽንሰ ሐሳባዊ ማህቀፋችን እንደተመለከትነው የምግባር መገለጫዎች መርሆዎች አንድም የአመለካከት፣ አንድም የድርጊት ናቸው። እንደ አመለካከት እነ «ፍቅርን» እና «እውቀትን» ማየት የሚቻል ሲሆን እንደ ድርጊት ወይም ውሳኔ ደግሞ «በጊዜ መከወን» እና «በእጅ መስራት» የሚሉትን ማዬት ይቻላል።

ያየናቸው ቁም ነገሮች እርስ በእርስ የሚናበቡ አንደኛቸው ላንደኛቸው መሰረት ወይም ቅድመ ሁኔታ የሆኑ ናቸው። ዋና ዋና የነገረ ግብረ ገብ መከራከሪያዎቹም ሦስት አንብሮዎችን (Thesis) እንደ መንገድ የሚጠቀሙ ናቸው። አንብሮዎችን እንመልከት

## 4.1. መስዋዕትነት

እስከ መቼ ድረስ? የትእግስት ልጓም! ዘላለም ትእግስት። ለሁሉም ነገር ትግስት። ክርስቶስም ትእግስቱን ጨርሶ በመስቀል ላይ ኤሎሄ ኤሎሄ ብሏል (1966፡6)

በዓሉ ግርማ በህዲስ አቀንቃኝነት በእነ ይርጋ ጸረ አቀንቃኝነት በ«የህሊና ደወል» ውስጥ የሚያንጸባርቀው የግብረ ገብ ፍልስፍና የመስዋትእነት (Altrustic Morality) ፍልስፍና ነው። ደራሲው በዓሉ ግርማ ሀዲስን የመስዋዕትነት ጉዞ ሲያስጉዘው መስዋዕትነቱን የተረዱትና የረዱት ዓይነት ሰዎች ለሀዲስ ቀርጾለታል።

ኤልያስ (2000) «ገጸ ክርስቶስ በበዓሉ ግርማ ቅድመ አብዮት ኖብል» በሚለው መጽሐፉ እንደሚጠቁመው አስቀድሞ «ሀዲስ» የሚል ስያሜን ማግኘቱ ያለምክንያት አይመስልም። በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ያስተማራቸውን የግብረ ገብ ፍልስፍናዎች የተዋረሰ መሆኑን ለማጠየቅም እንጅ። ሀዲስ በህሊናው ውስጥ ተሰንቅሮ የሚረብሸው አንዳች የአደራ ቃል አለ። ይህ የአደራ ቃል ክርስቶስ ወደ ምድር እንዲመጣ ካስገደደው የአደራ ቃል ጋር መሳ ለመሳ ነው። ያንን የአደራ ቃል የሚጠብቀው ሊድን የሚሻ አዲስ ትውልድ አለ፤ ክርስቶስ ነፍሳትን ከጨለማው ሲኦል እንደሚያወጣ ሁሉ ሀዲስ ደግሞ ነፍሳትን ከጨለማው ድንቁርና የማውጣት አደራ አለበት። «እጅህን በተስፋ ስጠባበቅ ቆዩሁ፤ አሁንስ ታከተኝ» (ገጽ 197) የሚለው የእናቱ ድምጸት ህሊናውን የሚሰረስረው ይህ አደራ ስላለበት ነው።

የሀዲስ እናት ልጃቸው ከጨለማ ወደ ብርሃን እንዲወስዳቸው ረጅም ዘመናትን በተስፋ ጠብቀዋል። ነገር ግን ተስፋቸውን እንደያዙ በአጸደ ሥጋ ተለይተዋል። ሀዲስ ጊዜው ሲደርስ አደራውን እንደሚወጣ ያውቅ ነበርና በእናቱ ሃዘን ለቅሶ የተቀመጠበት የህሊና ደወል ንባብ የለም። ይልቁንም እናቱን አደራ ለመወጣት እያንዳንዱን ቀን ይተጋል እንጅ። ስለዚህም እነ አቶ ይርጋ «ተረጋጋ» እያሉ የሚያነሱለትን ጥያቄ አይቀበልም። አስቀድሞ መስዋዕትነትን ለመቀበል ዝግጁ ነበርና። ይልቁንም መሰቀያውን ተሸክሞ ወደ ተራራው እየወጣ ነበር። ሀዲስ ሳህሌ የሚቀርጸውን አዲስ ዓለም ለመቅረጽ - እየቀረጸም ስለሚቀበለው መስዋዕትነት ራሱን አዘጋጅቶ ይገኛል። «በየትኛውም ዓለም ደልቷቸው የሚኖሩ አስተማሪዎች የሉም። ያስተማሪዎች ታሪክ ከሃዋርያት ጋር የተያያዘ ነው መሰለኝ። የእኛ ግን ይብሳል፤ ዝቅዝቅ መሰቀልና መወገር ነው የቀረን» (ገጽ፡8)

ክርስቶስ እንደ አሰተማሪ ደልቶት አልኖረም ወይም ሶቅራጥስ። ጳውሎስ እንደ መምህር ደልቶት አልኖረም ወይም ፕሌቶ። ወዲህ ደግሞ ሀዲስ ሳህሌ እንደማንኛውም መምህር ደልቶት እንደማይኖር ወይም ድሎትን መቋመጥ እንደሌለት ያውቃል፤ ያምናልም። «የእኛ ግን ይብሳል» ይላል። በሌላው አለም ካሉ መምህራን ጋር ሲነጻጸር አንድ የጨለማ አለም መምህር የበለጠ አብርኖትን ማስረጽ አለበትና የበለጠ መስዋዕትነትን ይጋፈጣል። ስለዚህም ነው «ዝቅዝቅ መሰቀልና መወገር ነው የቀረን» የሚለው። ወደ መሰቀያው ወደ መወገሪያው እየሄደ ይመስላልና።

ደራሲው በዓሉ ግርማ ይህን መስዋዕትነት በዋናው ገጸ ባሕርይ በኩል ሲያራምድ ሀዲስን እንደ ሰባኪ አይደለም ያመጣው፤ እንደ መምህር እንጅ። ምክንያቱም ሰባኪ ሆኖ ቃሌን እንጅ ተግባሬን አትከተሉ የሚል አይደለም፤ «ቃሉን ላካፍል» የሚልም አይደለም። ወይም መስዋዕትነትን ፍራቻ ከዘመኑ ጋር አብሮ እየዘመመና አብሮ እየቀና አልታየም። ከሀዲስ በተቃራኒ እነ አቶ ይርጋ የዚህኛው ጽንፍ ማንጸሪያ ሆነው ተስለዋል።

ለእነ አቶ ይርጋ ዓለም ማለት ይህ የተሰራው ዓለም ነው፤ የእሱንም ፍሬ እየቀጠፉ መመገብ ነው። ሌላ አዲስ ዓለም የመሥራት ወኔ የላቸውም። አብዝተው ስለ አዲስ ነገር አያስቡም፤ ካሰቡ እንኳ ያንን ዓለም ሌሎች እንዲሠሩላቸው ይጠብቃሉ። እምነት ይበቃል፣ በዓላትን ማክበር ይበቃል፤

የሚመጣው እስኪመጣ መጠበቅ እንጅ ተዘጋጅቶ መጠበቅን ገና አላወቁም። ስለዚያም ነው ችግር ማሳወቅን ችግር እንደመፍታት የሚቆጥሩት።

> አሁን ያሉት ስድስት ክፍሎች በተማሪዎች ብዛት ስለተጣበቡ በተጨማሪ ክፍሎች እንዲሠሩልን... ለሁለት መቶ ሰባ አምስት ተማሪዎች አራት አስተማሪዎች ብቻ በቂ ስላልሆኑ ተጨማሪ አስተማሪዎች እንዲላኩልን....አሁን ያሉት ክፍሎች ከማርጀታቸው የተነሳ መፈራረስ ስለጀመሩ ተጨማሪ አዲስ ክፍሎችን ለማሰራት ባይቻል እንኳ ያሉት እንዲታደሱልን....የማስተማሪያ መሳሪያ ስላለቁብን እንዲላኩልን....ደሞዝ በወቅቱ የሚደርስበት መንገድ ባስቸኳይ እንዲታሰብበት (ገጽ 8)

ይህና መሰል ጥያቄዎችና ማሳሰቢያዎች አቶ ይርጋ ለሰባት ዓመታት በደብዳዎች ሲጽፏቸው የነበሩ ናቸው። በአቶ ይርጋ እይታ አዲስ ዓለምን መሥራት አይቻልም፤ መጠበቅ እንጅ። ምክንያቱም መጠበቅ ምኞትን የሚያጎናጽፍ ሲሆን መሥራት ግን መሰዋዕትነትን የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ከመሥራት ይልቅ መጠበቅን መርጠው ደብዳቤ እየጻፉ ችግር ማሳወቅን የመፍትሔ ያህል ይጠቀሙበታል። ከአዲስ አበባ ለቀናት ተጓጉዞ ሱጴ የገባው ሀዲስ ግን አዲስ ዓለምን መሥራት እንጅ መጠበቅ አይገባም የሚል አቋም ማንጸባረቅ የጀመረው ብዙ ጊዜ ሳይወስድ ነው።

አቶ ይርጋ ትእግስት ያስፈልግሃል፤ ተረጋጋ እያሉ ለሚያነሱለት ጥያቄ መስዋእትነት ዛሬ እንጅ ነገ የለም የሚል አቋሙን ደጋግሞ ይነግራቸዋል። ይርጋ - ይርጋን (መረጋጋትን) ሀዲስ-ሀዲስን (አዲስ ዓለምን) ይሻሉ። ሀዲስ ነገሮችን ሁሉ ብቻውን ለመጋፈጥ (መስዋዕት ለመሆን) አይፈራም።

> ከብዙ ጠባያት ጋር የምውልበት በገሃነም አድርጌ መንግስተ ሰማያት ወጥቼ ነገስታት እልፍኞች አልፌ ከልዕልቶች ጋር ተሳስቄ ለምድር ከከበዱ ባለስልጣኖች ጋር ትከሻ ለትከሻ ተጋፍቼ አዎን .. ዳገት.. ቁልቀለት.. ገደል.. የብረት መዝጊያ .. አድማስ የማያግደው ዓለሜ ነው... ብቸኝነቴ። ብቸኝነቴን እወደዋለሁ....አብሮ አደጌን። አልፈራውም ... አልፈራውም ..እወደዋለሁ! (ገጽ 18)

ሀዲስ ብቸኝነቱን የሚወድደው ወደ አዲስ ዓለም የሚያደርገውን ጉዞ ስለሚወደው ነው። ሀዲስ ብቸኛ ነው። ብቸኝነቱ የመሪነት፣ ብቸኝነቱ የአስተዋይነት ነው። የሚመራን የሚከተል የአስተዋይን ሰው ሐሳብ የሚረዳ ደግሞ ጥቂትም ቢሆን ይኖራል። አዲስ ነገርን በአሮጌ አቁማዳ ማስቀመጥ የማይወዱ የሀዲስ ተከታዮች ብቅ፣ ብቅ የሚሉት ከዚህ ወዲያ ነው። ከእነዚህ አንዱ ፊታውራሪ ተካ ናቸው። ፊታውራሪ ተካ በሱጴ የተወደዱ ባላባት ናቸው። ምንም ያህል ዘመኑ የእሳቸውን አስተዳደር የማይፈቅድ ቢሆንም የአካባቢው ሰው ለአቤቱታ፣ ለብድር ወይም ለዳኝነት እሳቸው ጋ ይመጣል። የአካባቢው ሰው አብዝቶ ያከብራቸዋል። እኚህ የተከበሩ ሰው የሀዲስ ተከታይ፣ የሀዲስን ሐሳብ አራማጅ ሆነው ይመጣሉ። ለዚህ ማሳያው መስዋዕትነት የጊዜ ቅድመ ሁኔታን እንደሚፈልግ የሚነገረው በእሳቸው በኩል መሆኑ ነው።

> ከጊዜው ቀድሞ መገኘት ያስፈልጋል። ለጦርነት ያልተዘጋጀ የጦር አበጋዝ ሰራዊቱን ያስፈታል። ህዝብን ከጊዜ ጋር ያላራመደ መሪ ግዛቱን ያጣል። ሙሽራ ከመጣ በኋላ መንቃት መርበትበትን መርበድበድን ሚዛን ማጣትን አዎን እነዚህ ደግሞ ተደምረው ስህተትና ውርደትን ያስከትላሉ። ሁዋላ ክንፍ አውጥተው ቢሮጡ አይሆንም (ገጽ 32)

አንድን ሞት መስዋዕትነት የሚያሰኘው ከጊዜው አስቀድሞ ሲመጣ እንጅ የሰው ልጅ ከሞት ስለሚትርፍ አይደለም። መደበኛውን ሕይወት እነ አቶ ይርጋ እየኖሩት ይታያል፤ ይህ መደበኛ ሕይወት «እንደ ሰው» ወጥቶ መግባት፣ ከሞቀ ፍራሽ ላይ አለመንቀሳቀስ ነው። የዚህ ሂደት መጨረሻው «የእግዚአብሔር ሞት» ነው። «እዚህ እንደምታዬው የሁሉንም ፍላጎት ሊያረካ የሚችል ገንዘብና ጉልበት የለም። ህዝቡ ገንዘብም ጉልበትም የለውም» (ገጽ 10) የሚለው የአቶ ይርጋ መከራከሪያ «ባለንበት ተመችቶናል» የሚል ሙግት ነው። ይህ መከራከሪያ «ያለሁበት ተመችቶኛል» ለሚል መከራከሪያ የቀረበ ስለመሆኑ ተራኪው እንዲህ ይነግረናል፤

> ከእርሳቸው በቀር ትምህርት ቤቱን ለማሻሻል በሌሎች የሚደረገውን ማንኛውም ጥረት አቶ ይርጋ በጥሩ ዐይን አይመለከቱትም ነበርና የእሳቸውን ጥቅም ለመፈታተን የሚደረግ ሙከራ መሰላቸው (ገጽ 12)

ይህ የተራኪው (ደራሲው) ምስክርነት የህዲስን የመስዋዕትነት ጉዞ የሚያጎላምስ ነው። ሀዲስ አዲስ ትምህርት ቤት በማሰራት የሚያስተካክለው የግል ሕይወት የለውም። ነገር ግን አዲስ ትምህርት ቤት በመሥራት ትምህርት ያላገኙ ተማሪዎችን ለማስተማር፣ ሕይወታቸውን እንዲመረምሩ፣ ፍትኅን እንዲጠይቁ፣ መልካምና ክፉን እንዲለዩ ለማስቻል ነው የሚሠራው። የመስዋዕትነት ምግባር ቅድሚያ ለሌሎች መስጠት ነው። ከመስጠት ይገኛል እንጅ ከመስጠት ይጎድላል የሚል አይደለም።

## 4.2. «የፍቅር መሰላሉ እውቀት ነው»

በ«የህሊና ደወል» ውስጥ የምናዬው የግብረ ገብ ፍልስፍና የመስዋዕትነት ፍልስፍና መሆኑን ከላይ አየን። ይህ የመስዋዕትነት ምግባር ግን እንዲሁ የሚገኝ እንዳልሆነ ታሪኩና ገጸ ባህርያት ይሞግታሉ። ይልቁንም መስዋዕትነት ከፍቅር የሚገኝ እንደሆነ በመሞገትም እንጅ። ሀዲስ ለሱጴ አዲስ ትውልድ መስዋዕት ለመሆን ሲነሳ ከፍቅር የተነሳ ነው። እዚህ ጋ መነሳት ያለበት ጥያቄ ይህ ፍቅር ከየት ይገኛል? የሚል ነው። በየህሊና ደወል ውስጥ የፍቅር ምንጩ እውቀት መሆኑ ይነገራል። ያለ እውቀት በቀር ፍቅርን የሚያውቅ፣ ያለ ፍቅር በቀር መስዋዕትነትን የሚሻ የለምና።

> የፍቅር መሰላሉ እውቀት ነው-የእውቀት መሠረቱ ደግሞ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤት አዲሱ ቤተግዜር ነው የምለው ስለዚህ ነው። ያለ ፍቅር ህይወት ትርጉም የላትም። ህልውና ባዶ፤ የሚጮህ ናስ ወይም የሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ትሆናለች-ያለፍቅር (ገጽ145)

በዚህ መከራከሪያ ማስረጽ የተፈለገው ነጥብ የርትዕ ምግባር ፍልስፍና አራማጆች እንደሚሉት መልካምነትና እኩይነት ተፈጥሯዊ ሳይሆኑ ራስ ሰራሽ መሆናቸውን ነው። እኩይ የቱ ነው? መልካምስ የቱ ነው? የሚለውን ለመለየት የሚያስችለው ጥበብም እውቀት ይባላል የሚል ነው። «አዲሱ ቤተግዜር» የተባለውም ትምህርት ቤት ነው። «እግዚአብሔር መልካም ነው» ከሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባል በመነሳት ደራሲው መልካምነትን ከእግዚአብሔር ጋር አገናኝቶታል። «ክርስቶስም ቢሆን በመሰረቱ በመስቀል ላይ ተቸነከረ የሚባለው ስለፍቅር በፍቅር ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መሰረቱ ይኸው ነው» (ገጽ145)

የእግዚአብሄር መገኛ ደግሞ ትምህርት ቤት መንገዱም እውቀት (ትምህርት) መሆኑን ነው የሚናገረው። ይህ «ቤተግዜር» ከማንም የሚጠበቅ ሳይሆን በራስ የሚሠራ ነው። ፍቅርን ከየትኛውም ዛፍ ላይ መሸምጠጥ የሚቻል አይደለም፤ ከራስ ሥራ ላይ እንጅ። ይህ አቋም በመጽሐፉ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተለይ በሀዲስና ፊታውታውራሪ ተካ በኩል ሲገለጽ ይታያል። ሀዲስ ተስቦ በተባለ በሽታ ተጠቅቶ አልጋ በያዘበት ጊዜ በሰው ሸክም ይንቀሳቀስ ነበር። ታዲያ አንዴ በአልጋ ተሸክመው በሚወስዱት ጊዜ እየተገነባ የነበረው ትምህርት ቤት አካባቢ ሲደርስ ያለ የሌለ ጉልበቱን ተጠቅሞ ቀና ብሎ ትምህርት ቤቱን ያየዋል፤ ከዚያም መልሶ ጋደም ይላል። ይህን ያስተዋለ የጤና ባለሙያ በአግራሞት እንዲህ ይላል፤

> ትምህርት ቤቱን እንደዚያ ትኩር ብሎ ሲመለከት ባየሁት ጊዜ የሚያመልከው መስሎኝ ነበር። ውነትም ደግሞ በእጅ እየሠሩ ለዚህ ህዝብ መስዋዕትነት ምን እንደሆነ ማሳዩት አዲሱ አምልኮት መሆን አለበት (ገጽ 229)

እውቀት የፍቅር መንገድ ፍቅር የመስዋዕትነት መንገድ ሆነው ተስለዋል። በዚህ የግብረ ገብ ዕይታ መሰረት ሰዎች ካላወቁ ፍቅርን ሊረዱት አይችሉም፤ ፍቅርን ካልተረዱት «መልካም ሰው» መሆን አይችሉም። የመልካም ሰውን ትሩፋትም ሊያደርጉ አይችሉም። ይህ ወደ መልካምነት የሚደረግ ጉዞ በራሳቸው በሰዎቹ የግል ጥረት የሚመጣ ነው። ወይም መስዋዕትነት እየከፈሉላቸው ያሉ ሰዎችን ፈር በመከተል።

ይህንን መከራከሪያ ለማጽናትም በተለያዩ ጊዜያት ደራሲው አስረጅዎችን ያሳያል። ለምሳሌ ፊታውራሪ ተካ ዘንድ ቀርበው መበደላቸውን እየተረኩ የእርዳታ ተማጽኖ ከሚያደርጉት አንዱ የመልካም ነገሮች መገኛ ትምህርት መሆኑን ጠቆም ያርጋሉ።

> ከሰባቱ ልጆቸ አምስቱ ለትምህርት የደረሱ ናቸው። በቂ ክፍል የለም ስለተባልኩ የሰው ከብቶች ሲጠብቁ ነው የሚውሉት። ትምህርት ቢያገኙ በማን እድሌ። ከተማሩልኝ እኔንም ከዚህ የኑሮ ስቃይ አንድ ቀን ያወጡኝ ይሆናል የሚልም ተስፋ አለኝ። ይሄንን እንደ እዳ አልቆጥረውም (ገጽ 61)

ይህ መከራከሪያ ትምህርት ወይም እውቀት ለኢኮኖሚ እድገት የሚኖረውን ሚና ለመናገር የቀረበ ይመስላል። ቁምነገሩ መልካምነትንና እኩይነትን ስለመለየት ነው። ከዚህ የገበሬው ንግግር በፊት እንዲህ የሚል ንግግር አለ «....ከእግዜሩ የምንታረቅበት መንገድ አጣን እንጅ፤ እግዜሩ ነው የተጣላን» (ገጽ 61)።

ይህን ንግግር የሚናገሩት ኑሯቸው በመቃዎሱ ነው፤ የኑሯቸው መቃወስ ምክንያቱ ተደራራቢ ወጭ ነው። የተደራራቢ ወጭ ምክንያቱ የሰዎች ጭካኔ እና ተንኮል ነው። የሰዎች ጭካኔና ተንኮል ምክንያቱ የትምህርት እጥረት ነው፤ የትምህርት እጥረቱ «የቤተግዜር» ችግር ነው። የቤተግዜር ችግር ደግሞ የእውቀት ችግርን ፈጠረ። በየህሊና ደወል ውስጥ የሚታዬው የመጀመሪያው አንብሮ መስዋዕትነት ሁለተኛው አንብሮ ደግሞ እውቀት ነው። መልካምነትና እኩይነት የእምነት ውጤት ነው፤ እምነት ሥልጣኔ ነው[4] ሥልጣኔ የሚገኘው ከእውቀት ነው።

ይህ ክርክር በሌላም አስረጅዎች የተደገፈ ነው። ከአንጓማሽ ገጸ ባህርያት መካከል ብዙውን ጊዜ የሀዲስ ደጋፊ ሆነው የሚቆሙት፣ አቋሙን አቋማቸው አድርገው የሚሟገቱለት ፊታውራሪ ተካ ናቸው። ከፊታውራሪ ተካ ትይዩ በሥልጣን፣ በገንዘብ፣ በዝና እና በተደማጭነት ተገዳዳሪ የሆኑ ሌላ ፊታውራሪ አሉ። ፊታውራሪ አያና አቋማቸው፣ ፍልስፍናቸው ሁሉ ሀዲስና ፊታውራሪ ተካ ከሚያራምዱት በተቃራኒው ነው። ፊታውራሪ ተካ እንደ ሀዲስ ሁሉ እውቀት፣ ፍቅር፣ ትብብር፣ መስዋዕትነት የመልካምነት መገለጫዎች ናቸው ብለው ያምናሉ። ፊታውራሪ አያና ግን

> ...የገንዘብ ሃይል የበለጠ ስልጣንና ክብር ያስገኛል ብለው ማመን ስለጀመሩ ገንዘብ አውጥተው የሰጡ እንደሆን ስልጣናቸውን ያካፈሉ ይመስላቸዋል። ከእግዜር በታች ሌላው ትልቅ ሃይል ገንዘብ ነው። ገንዘብ አፍ አለው ይናገራል። ገንዘብ ጆሮ አለው ይሰማል። ስልጣኑም አይበገርም። ቃሉ ከመሬት አይወድቅም ማለትን ያዘወትራሉ (ገጽ 73)

ደራሲው በዓሉ ግርማ ፊታውራሪ አያናን በዚህ መልኩ ሲስላቸው በትክክል ከፊታውራሪ ተካ የሚቃረን አመለካከት እንዳላቸው ለማሳየት ነው። በፊታውራሪ አያና እምነት ውስጥ የሚንጸባረቁ የትኩረት ነጥቦች ደስታ፣ ምኞት፣ እርካታ፣ ሥልጣን፣ ገንዘብ እና ኃይል ናቸው። እነዚህ የትኩረት ነጥቦች ከመስዋዕትነት የግብረ ገብ ፍልስፍና በተቃራኒ የሚቆሙ ናቸው። ፊታውራሪው ደስታን ለማግኘት የሚሞክሩት ጭካኔ ውስጥ ነው። ከእስር የሚፈቱት ያሰኛቸውን ነው እንጅ ፍትኅ የሚገባውን አይደለም። ያሰኛቸውን በመፍታት ደስታን ይቃርማሉ። ያስቆጣቸውን ይገርፋሉ እንጅ ስለጥፋቱ አይደለም፤ ያስቆጣቸውን በመግረፍ ደስታን ያባርራሉ። የሚያስተዳድሩበት ሕግ የሚመነጨው ከእውነት ሳይሆን ከገዛ ምኞታቸው ነው። ምኞታቸው ደግሞ ደስታን መፈለግ፣ ሥልጣንን ማረጋገጥ፣ ኃይልን እየተጠቀሙ ለእርካታ መማሰን ነው።

---

[4] ሽብሩ ተድላ (2011) ‹ከየት ወደ የት?›› የሰው ዘር ዝግመተ ለውጥ እና ማኅበራዊ እድገት ያለመቋረጥ ይጓዛል በሚለው መጽሐፋቸው «የሰው ልጅ የማይታይ፣ የማይዳሰስ፣ «አካል» አለ ብሎ ማመን ከጀመረ ወዲህ ያንን አይነት እምነት እየተለመደ ሄደ፡፡ ያም ከተሞክሮ ሊመነጭ ወይም ከእምነት ጋር የተቆራኘ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ባልታዩ ባልተዳሰሱ «አካላት» ማመን የሰው ልጅ ልዩ ባህርይ እንደሆነ ይገመታል» (ገጽ13) ይላሉ፡፡

በተቃራኒው ፊታውራሪ ተካ የደስታ ምንጩ መልካም ተግባር መሆኑን፣ የሀዲስን በጎ ተግባራት እውቅና በመስጠት ይመሰክራሉ።

> ስለችግር ከማውራት - ብዙ ከመተቸት- ትንሽ ሥራ መሥራት ጠንካራ እምነትን ይጠይቃል። በመንፈሳቸው የጸኑ ጠንካራ እምነት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ካልተገኙ መሻሻል ጭራሹኑ እየራቀ ይሄዳል። ልጅ ሀዲስ ተጨማሪ የትምህርት ክፍሎች ለመሥራት ብቻውን መፍጨርጨር ከጀመረ ቆይቷል። ደቀ መዝሙሮቹ እኛው መሆን አለብን። ይህ ድግስ የእሱ ደቀመዝሙሮች እንድንሆን ካደረገን የበለጠ ቁም ነገር አተረፈ ማለት ነው። ሥራው ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለልጅ ልጆቻችን የብርሃን ሀውልት ሆኖ ይኖራል። ያዲሱ ትምህርት ቤት ሥራ ከፍጻሜ እንዲደርስ እግዚአብሔርን እንለምነው (ገጽ 123)

የፊታውራሪ አያና የግብረ ገብ ፍልስፍና ግላዊ ደስታን ወደሚያመጣ መንገድ መጓዝ፣ የግል ደስታንና እርካታን በሚያረጋግጥ መንገድ መጓዝ ነው። ግቡም ደስታን እና እርካታን ማጣጣም ነው። ይህ ደስታና እርካታ በአንድ ቅድመ ሁኔታ ላይ ብቻ ይመሰረታል። የፊታውራሪ አያናን ምኞት እስካሳካ ድረስ ብቻ። በተቃራኒው ከሀዲስ ጎን ያሉት ፊታውራሪ ተካ የራስን ሳይሆን የወል ደስታን መፈለግ ላይ የተመሰረተ ፍልስፍና ነው ያላቸው። ከመተቸት፣ ችግርም ከማውራት መሥራት የበለጠ ቁም ነገር እንደሆነ ይሰብካሉ። ጠንካራ እምነት ይዞ ለሥራ የሚነሱ ካልኖሩ በቀር፣ እነዚህን ጥቂቶችንም የሚደግፍ ብዙሀ ካልኖረ በቀር ማኅበረሰብ ጨርሶ ሊሻሻል እንደማይችል ይናገራሉ። እዚህጋ ቅድመ ሁኔታው የማኅበረሰብ አዎንታዊ ለውጥ እንጅ ግለሰባዊ ደስታ ወይም ምኞት አይደለም። የፊታውራሪ ንግግር ከሀዲስ ፍልስፍና ጋር ስሙር መሆኑን ወደ ገጽ 111 ተመልሰን እንመልከት። ሀዲስ እንዲህ ይላል፤

ታዲያ ወደፊት ልንራመድ የምንችለው በወሬ- በፍልስፍና-በሥራ በማይገለጥ የመጽሐፍ እውቀት አይደለም። ሥርየታችን ሥራ ነው። ማህሌት ቆሞ በማደር፤ ቤተመቅደስን በማጠን -በጾም በጸሎት ብቻ አይደለም። ሥልጣን ይዞ በመኮፈስ-ስልጣንን እንደ እውቀት በመቁጠር - ስልጣንን እንደ አላፊነት ሳይሆን እንደ መብት በማዬት አይደለም። በስልጣን ሰገነት ላይ ወጥቶ ከህዝብ ትንፋሽ በመራቅ እንደኮከብ እያንጸባረቁ በመቀመጥ- የህዝብ እንባ ከማይደርስበት ቦታ - በሥራ እንደገና መወለድ ያስፈልጋል። የዘመኑ ጀግና ሰራተኛ ነው። ሥራ ስሩ ብሎ መለፈፍ ብቻ አይበቃም። ሰርቶ ማሳየት ያስፈልጋል። ትችት ብቻውን የአእምሮ መካንነት-የወኔ ማጣት ምልክት ነው። በርግጥ ይህ የሀዲስ ንግግር ወደ ሦስተኛው አንብሮ የሚመራን ነው።

## 4.3. አንብሮ ሦስት፡ ሥራን በጊዜ

«የሀሊና ደወል» ደግ ምግባር ብሎ የሚያስቀምጠው የፍልስፍና መንገድ ከእንስሳት የሚለየው እምነት መሆኑን ያወቀና የእኔ የሚለው እምነት ያለው፤ እምነቱ ደግሞ ህሊናውን ወደ መልካም የሚመራው መሆኑን ያወቀ፣ ህሊናን ወደ መልካም የሚመራው ፍቅርን ገንዘብ ማድረግ መሆኑን የተረዳ፣ ፍቅርን ገንዘብ ለማድረግ እውቀት መሰረት መሆኑን የሚቀበል ሰው ነው። ነገር ግን

እነዚህ ሁሉ የመልካምነት መንገዶች እንጅ መልካምነት እንዳይደሉ ሦስተኛው አንብሮ ይሞግታል።

በተግባር የማይገለጽ መልካምነት ከንቱ መሆኑን በመጽሐፉ የተለያዩ ክፍሎች ያትታል። ለምሳሌ ሀዲስ ብቻውን እውቀት ወይም መልካም ማሰብ የመልካም ምግባር መገለጫ ሊሆን እንደማይችል እንደሚከተለው ይሞግታል፤

> ከብዙ አሳብ ትንሽ ሥራ ይበልጣል ብዬ ነው። እግዜር ለሰው ከሰጠው ትልቅ መሳሪያ አንዱ እጅ ነው። ግን ባገራችን በእጅ የሚሰራ ሰው እስካሁን በወራዳነት ሲታይ ቆይቷል....ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ የምትፈልገው የሚሰራ እጅ ነው (ገጽ104)

አንድ ግለሰብ ጥሩ ተማረ፣ ጥሩ ሰው ነው፣ ጥሩ እውቀት አለው፣ ለሰዎች ከበሬታ አለው ወዘተ. የሚሉ ቅጥያዎች ቢኖሩት እነዚህ ከፍልስፍና አንጻር የእውነትነት ዋጋቸው (Truth value) በምን ይለካል? የሚል ጥያቄ ይከተላል። ወይም አንድ የምግባር ፍልስፍና መንገዱን ብቻ አሳይቶ ውጤቱን ካልጠቆመ በቀር ወይም ውጤቱን ነግሮን መንገዱንም ካልጠቆመን በቀር የተሟላ የግብረ ገብ ፍልስፍና አለው ለማለት ያስቸግራል። በ«የህሊና ደወል» ውስጥ የዚህ ማሰሪያ ሆኖ የሚመጣው ይህ ሦስተኛው አንብሮ ነው። ሰው በህሊናው ያሰበውን መልካም ይሁን መጥፎ የሚተገብረው በእጁ ነው። እጅ የመጨረሻው ጉዳይ ፈጻሚ ሆኖ ነው የቀረበው።

ሀዲስ ህሊናውን በእምነት ፍቅሩን በእውቀት ያነጸ ወይም ማነጽ የሚፈልግ መሆኑን ይገናራል። ‹አውቃለሁ» ብሎ ከመናገር ወይም «ያውቃል» ተብሎ ከሚነገርለት ይልቅ በእጁ መሥራትን እንደሚመርጥ ይናገራል። አንድ ሰው ጥሩ ትምህርት ያለው መሆኑ የሚታወቀው የተማረውን በእጁ መሥራት ሲችል ነው፤ ቃል በቃል ቢያነበንበው ልክ አይደለም የሚል አቋም አለው ሀዲስ ።

ካህናት ስለ ፍቅር ይሰብካሉ፣ ፍቅርን ካልኖሩት እንዴት ጥሩ ምግባር አላቸው ልንል እንችላለን? ኮሌጅ ገብተው ግብርና ያጠኑ ተማሪዎች አፈርን ይጸየፋሉ፣ እንዴት ጥሩ ሰዎች ናቸው ማለት ይቻላል? የሀዲስ መንገድ ይህ ነገሮችን በእጅ መሥራት ወይም በተግባር መግለጽ ብቻ ላይም የሚመሰረት አይደም። ያ የሚሠራው ያ በእጅ የሚደረገው ነገርም ውጤቱን መልካም ወይም መጥፎ ብሎ ለመበዬን መሰረት ይሆናል።

በሀዲስ እይታ መጥፎውን ማፍረስ መልካም የግብረ ገብ መንገድ አይደለም ይልቁንም መልካሙን መሥራት እንጅ። ለበቀል ከመራመድ ለይቅርታ መራመድ፣ ከብዙ ወሬ ትንሽ ሥራ፣ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅርን የመረጠና የተገበረ ሰው ነው የመልካም ምግባር መገለጫው። ሀዲስ አሮጌውን ትምህርት ቤት እናፍርሰው ሲል አይደመጥም፤ አዲስ ትምህርት ቤት እንሥራ ይላል። አቶ ይርጋ ሥራውን እያደናቀፉበት «ይወገዱልኝ» የሚል ምኞት ሲይዝ አይታይም፤ይልቁንም እንተባበር የሚል ጥሪ ያርብላቸዋል።

በእጅ መሥራት፣ እጅን ለበጎ አላማ መጠቀም ጠቅላላው የግብረ ገብ ፍልስፍና ማስረጃ ሆኖ ሲመጣ እንዲያው ብልጭ ብሎ የመጣ አይደለም። እንዲያውም የታሪኩ አጽም የተገነባው «በእጅ» ላይ ስለመሆኑ የመጽሐፉ መነሻና መድረሻ ይነግረናል። የሀዲስ እናት ነፍሳቸው ከስጋቸው ልትለይ በተቃረበች ጊዜ እንዲህ ይሉታል።

> እጅ እጅህን ስጠብቅ ኖርኩ። እጆችህ ጡቶቼን ይዘው መጥባት ከጀመርክ ጊዜ አንስቶ የምሽት ቀን አለኝታዎቼ ናቸው እላቸው ነበር። ደከምኩ ልጄ በቃኝ መሰለኝ... (ገጽ 197)

ሀዲስ ከዚህ ወዲያ ነው ለእናቱ ያልደረሰ እጁን ለሀገሩና ለወገኑ ለማድረስ የተነሳው። በእናቱ ጊዜ አንድ ስህተት ነበር፤ ጊዜን አለመጠበቅ። አሁን እጁ ሥራን ስትሰራ ጊዜን ታሳቢ አድርጋ መሆን እንዳለበት አደራ አለበት። የመልካም ምግባር መገለጫው ለአደራ በቅቶ መገኘት ነው። ሀዲስ አደራውን ለመወጣት ራሱን ከጊዜና ከእጅ ተግባር ጋር ያስተሳሥራል።

## 5. ማጠቃለያ

በ«የህሊና ደወል» ውስጥ ያለው የግብረ ገብ ፍልስፍና እንደ ጽንሰ ሐሳብ ካየናቸው ልዩ ልዩ ዓይነት የግብረ ገብ ፍልስፍናዎች ውስጥ ከእኔያዊ (Ethical Egoism) በተቃራኒ ያለው የመስዋዕትነት ግብረ ገብ (altruistic morality) ጋር መሳ ለመሳ ነው። በዓሉ የመስዋዕትነት ግብረገባዊ ፍልስፍናን ለማስረጽ ሦስት አንብሮዎችን ተጠቅሟል። የመጀመሪያው አንብሮ በፍቅር የሚገለጽ መስዋዕትነት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወደዚህ መስዋዕትነት የሚያደርሰው የፍቅር መሰላሉ እውቀት ነው የሚል ነው። ሦስተኛው ደግሞ ወደ መስዋዕትነት የሚያደርሰው ፍቅርም በጊዜ በሚከወን ተግባር መታገዝ አለበት የሚል ነው። ይህ የግብረ ገብ ፍልስፍና በአንዳንድ ፈላስፎች በተለይም በእኔያዊ (Ethical Egoism) ፍልስፍና አራማጆች ዘንድ እንደ የዋህነት ወይም የደመ ነፍስ ግብረገባዊት ተብሎ ሲገለጽ በሌሎች እይታ ደግሞ የመስዋዕትነት ግብረ ገብ ለብዙሃኑ ደስታ ወይም ጥቅም መሆኑን ይሞግታሉ።

ከመስዋዕትነት ፍልስፍና በተቃራኒው ያሉ ፈላስፈፎች ከሚያነሷቸው ጥያቄዎች ቁልፍ ሊባል የሚችለው ራስን ሳይጠቅሙ ለሌሎች ጥቅም መሥራት ግብረ ገባዊነት ሳይሆን ደመነፍሳዊነት ነው የሚል ነው። በመሠረቱ ደመነፍሳዊነት መገለጫው ምንድን ነው ብሎ ማየት የሚገባ ነው። ሰው አሳቢ ፍጡር ነው ሲባል አመክንዮን ይጠቀማል። ወይም በሌላ አባባል የሰው ልጅ መገለጫው አመክንዮ ነው። ደመ ነፍስ የእንስሳት መገለጫ ነው። ከዚህ አንጻር በ «የህሊና ደወል» ውስጥ የተንጸባረቀው የመስዋዕትነት ፍልስፍና አመክኗዊ አይደለም ብሎ መከራከር ይቻላል ወይ? በዚህ አጥኝ እይታ ይህ ክርክር የሚያዋጣ አይደለም። ራሱ የመስዋዕትነት ግበረገባዊ ፍልስፍናው የተዋቀረው በአመክንዮ ነው። በዚህ ትንታኔ ለማየት እንደሞከርነው «የህሊና ደወል» የመስዋዕትነት ግብረ ገባዊ ፍልስፍ በሚከተለው አመክንዮ ላይ የተመሰረተ ነው።

ሰው አሳቢ ነው፤ ስለዚህም ኅሊና አለው። ሰው መሠልጠን እንደሚችል ያምናል፤ ስልዚህም እምነት አለው። ሰው ፍቅር እምነትን እንደሚገነባ ያውቃል፤ ስለዚህም እውቀት አለው። ሰው ትምህርት እውቀትን እንደሚሰጥ ያምናል፤ ስለዚህም ትምህርትን ይቀበላል። ሰው ሊሞትለት፣ ሊንገላታለት፣ ሊገለልበት የሚያስችለው እምነት ያስፈልገዋል፤ ይህም በትምህርት ይገኛል። መስዋዕትነት የራሱን ጊዜ የሚፈልግ ተግባር ነው።

በዚህ አመክንዮ ቅደም ተከተል የመስዋዕትነት ግብረገባዊ ፍልስፍና የደመ ነፍስ ሥራ ነው ሊያሰኝ የሚያስችል አይደለም። ምክንያቱም ፍቅር እምነትን እንደሚገነባ፣ እምነት ህሊናን እንደሚመራ፣ ይህንንም በመማር ማወቅ እንደሚቻል የተረዳ ሰው አመክኗዊ እንጅ ደመ ነፍሳዊ ሊባል አይችልም። በተጨማሪ አንድ ነገር በጊዜው መሰራት እንዳለበት የሚያውቅ ሰው ማለት ነገሩ ያለ ጊዜው ከተሠራ የደመ ነፍስ ሥራ መሆኑን ያውቃል ማለት ነው። የደመ ነፍስን ሥራ አውቆ የፍልስፍና አንጓን የፈጠረ ደመ ነፍሳዊ ሊባል አይችልም።

## ማጣቀሻዎች

**ቀዳማይ ምንጭ**

በዓሉ ግርማ (2005) *የህሊና ደወል።* 3ኛ እትም። ማንኩሳ ማተሚያ፣ አዲስ አበባ።

**ካላዓይ ምንጮች**

ሽብሩ ተድላ (2011) *ከየት ወደ የት? የሰው ዘር ዝግመተ ለውጥ እና እድገት ያለመቋረጥ ይጓዛል፤* ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

ኤሊያስ አያልነህ፣ *ገጸ ክርስቶስ በበዓሉ ግርማ ቅድመ አብዮት ኖብል፣* አርቲስክ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ በባ፣ ኢትዮጵያ፣ 2000።

ቴዎድሮስ ገብሬ (2001) "የአማርኛ የርእይ መነጠቅ ልብወለዶች" *በበይነ- ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ* አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡

ጠና ደዎ (2008) *ሰው ግብረገብና ሥነ ግበረ ገብ ፡ የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች፣* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ፣ አዲስ አበባ

Bernstein J.M (1992) *The fate of Art: aesthetic alienation from Kant to Derrida and Adorno,* the Pennsylvania state university press, USA

Sidgwick, H. (1874). *The Methods of Ethics* (7th ed.). Macmillan.

Hobbes, T. (1996). *Leviathan* (R. Tuck, Ed.). Cambridge University Press. (Original work published 1651.

Kant, I. (1998). *Groundwork of the metaphysics of morals* (M. J. Gregor, Trans.). Cambridge University Press.

Moran J. (2002*) Interdisciplinarity,* published by Routledge, London and NewYork

Plato v. Disputatio, *On the Aesthetic Constitution of Moral Virtue and the Justification of Aesthetic*, Obligations, Creative Commons Attribution-Noncommercial-No Derivs 3.0 License, Vol. XIII, No. 62, December 2021 ©2021

Rand A (1964) *The virtue of selfishness; a new concept of egoism,* Signet book, New American Library, New York.

Rachels, J., & Rachels, S. (2003). *The elements of moral philosophy* (5th ed.). McGraw-Hill.

https://plato.stanford.edu/entries/ethics-virtue/ Rosalind Hursthouge (1998) *Virtue Ethics*, Stanford encyclopedia of Philosophy (online published) visited Augst 7-2025.

Shafer-Landau, R. (2015). *The fundamentals of ethi*cs (4th ed.). New York, NY: Oxford University Press.

Sidgwick, H. (1907). *The methods of ethics* (7th ed.). London, England: Macmillan.

Tena S. (2008) (Unpublished), *The changing face of moral vision in Amharic novel*, Ph.D dissertation, English Literature, college of eduactiona and behavioral studies, AAU.

William F. (1973). *Ethics* (2nd ed.). Englewood Cliffs, NJ: Prentice-Hall.